ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

Coalition for Unity and Democracy Party
(Kinijit)

# የቅንጅት አለማቀፍ የፖለቲካ አመራር ኮሚቴና የአውሮፓ የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች ተወካዮች እ.ኤ.አ ከመስከረም 15-17 2006 አ.ም በቤልጂም ሉቨን ከተማ ባደረጉት ስብሰባ ማጠቃልያ የወጣ የአቋም መግለጫ

የስብሰባው ዓላማ፣- ቅንጅት ያለበትን ችግር በሚገባ ተረድቶና አቅምን አስተባብሮ ቀልጣፋና አፋጣኝ ስራ ለመስራት ያስችለው ዘንድ ያለመ ነበር። ይህንን አላማ ከግቡ ለማድረስ በሚቀጥሉት ነጥቦች ላይ ሰፊ ውይይት ተደረገ።

- የቅንጅትን መሰረታዊ የፖለቲካ መርሆዎችና ራእዮች
- የሰላማዊ ትግሉ ሂደት በቀጣይነት
- በቅንጅት አለም አቀፍ አመራር አመሰራረትና አሁን የሚገኝበት ይዞታ
- ለአለም አቀፍ የቅንጅት አመራር የድርጅት ጉዳይ ኮሚቴ የውጪውን አደረጃጀት በሚመለከት በቀረበው የውይይት ሰነድ ላይ
  - የድጋፍ ድረጅቶች ሚና ከቀረበው ሰንድ አንጻር
  - ቅንጅት እንደ ፓርቲና የድጋፍ ድርጅቶች ሚና
  - አሳታፊነት፣ ዲሞክራሲያዊ ውክልና
  - አንድ ወጥ ያአባላት አመላመልና የገንዘብ አያያዝ
  - አለም አቅፍ ያማካሪወች ሸንጎ
  - ያውሮፓ ካውንስል የተመሰረትባቸው አላማውችና ያለማቀፍ አመራር መፈጠር

ትብብር ለነጻነት ለዲሞክራሲ አመሰራረት በሚመለከት

- በማንዴት ጥያቄ ላይ
- ለምን አላማ
- ጠመንጃ ያነሱ ድርጅቶችና ቅንጅት
- የውቅቱ ህገመንግስት ጥያቄ ና ትብብሩ
- በትብብሩ አባል ድርጅቶችና በኤርትራ መንግስት መሃል ስላለዉ ግኙኝነትና ይህም ሊያሳድር የሚችለዉ ተጽእኖ
- አሁን ትብብሩ ያለበት ሁኔታ
- የቅንጅት ቦታ በትብብሩ ውስጥ
- መደረግ ስለሚገባችው ጉዳዮች
- ትብብሩ ዘላቂ የሰላም ያንድንትና ያዲሞክራሲ ጥያቄወችን በመፍታት ስለሚኖረው ፋይዳ

በዚሁ ውይይት ላይ በቅንጅት አለም አቀፍ አመራር ኮሚቴንና ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ አመሰራረት ላይ ግልጽ ግንዛቤ ያላግኙ ተሳታፊወች ባቀርቧቸው ፣

- ቅንጅት በሰላማዊ ትግል የሚያምን ሆኖ ሳለ የትጥቅ ትግል ከሚያካሂዱና በጎሳ ከተደራጁ ይልቁንም ኢትዮጵያዊነትን ሲያውግዙ ከኖሩና ዛሬም በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የጠራ አቋም ከሌላችው

ድርጅቶች ጋር ትብብር መድረጉ ፣ በትብብሩ ውሳኔ አሰጣጦች ላይ የቅንጅት አቅም ወይም የሚኖረው ድርሻ፣ ቅንጅት ጠንካራ ድርጅት ሆኖ ሳለ እንደሌሎች እንደ አናሳ ድርጅት ተቆጥሮ ባንድ ድምጽ ብቻ መውከሉ፣ አንድ አይነት አመለካከትና አደረጃጀት ባላቸው ድርጅቶች በድምጽ አሰጣጥ ላይ ሊያሳድሩ የሚችሉት ተጽእኖ ከግንዛቤ ውስጥ ስላለመግባቱ ያሳደረባችውን ስጋትና ቅሬታ በስፋት በማቅረብ ሰፊና ነጻ ውይይትና ክርክር የተካሄደበት ነበር። በቀረቡት ጥያቄወች፣ ይከሰታሉ በማለት በቀረቡት ስጋቶችና ችግሮች ዙሪያ  ከበቂ በላይ በመነጋገር ሁሉም ነገር ተሰብሳቢወቹ በሙሉ በሚመኙት የተስተካከለና የጠራ ደረጃ ባይገኝም ወደፊት በሂደት ሊታረሙና ሊስተካከሉ የሚችሉ ጉዳዮች መሆናችውን  በመተማመን የውይይቱ ተሳታፊወች ተፈጥሮ የነበረውን የፖለቲካ አመራር ክፍተት ለመሸፈን በቅርቡ የተደራጀውን የቅንጅት አለማቀፍ አመራር ኮሚቴንም ሆነ ለሰላምና ለዲሞክራሲ ግንባታ ዋስትና ይሆናል የትባለለትን "ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲን" ሙሉ ድጋፍ በመስጥት ለማጠናከር ከስምምነት ላይ ደርሷል

በዚህም መሰረት እ.ኤ.አ ከመስከረም 15-17 2006 ባካሄድነው ሰፊና ጥልቅ ውይይት

1. ወያኔ በወሰደው እመቃ እና አሁንም ተንሰርፍቶ በሚገኘው የወያኔ ህገወጥነት የተነሳ የዛች ሃገር የቁርጥ ቀን ልጆች የሆኑና በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ በሃቅ የተወደዱ የተከበሩና የተፍፈቀሩ መሪዎቻችን፣ የህዝብ አንደበት ሆነው መስዋእትነት ሲከፍሉ የኖሩ የነጻው ፕረስ አባላትን እና የሲቪክ ማህበራት ተወካዮችን እና የቀሩትንም የህሊን እስረኞች እንዲፈቱ ጫና ሊያሳድር የሚችል የትግል ስልት በማጠናከር ያላሳለሰ ጥረት ማድረግ
2. የአውሮፓ ፓርላማን ማእከል ያደርገና እያንዳንዱ አገር የሚመለከት የዲፕሎማሲ ስራ ማስጀመር እና በስፋት መቀጠል
3. የድጋፍ ድርጅት በሌለባቸው የኢትዮጵያውያን ክምችት ያለባችውን አገሮች ባጭር ጊዜ ውስጥ አመቺ ሁኔታን በመፍጠር ምስረታውን ማካሄድ
4. በህዝብ ግንኙነትና በፕሮፖጋንዳ በኩል ሁሉንም የሚዲያ ስልቶች በመጠቀም ሰፊ የመርጃ እና የህዝብ ግንኙነት ስራ በከፍተኛ ደረጃ ተደራጅቶ እንዲሰራ
5. በየአገሩና በአህጉሩ ካሉ የሎቢ አድቮካሲ ቡድኖች የሲቪክ ማህበራትና ሌሎችም የድጋፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር መስራት
6. በአውሮፓ ደረጃ የቅንጅትን የፖለቲካ ስራና የድጋፍ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ የሚያስተባብር አንድ ጽህፈት ቤት ባስቸኳይ እንዲቋቋም
7. በሃገሪቱ ጉዳይ ላይ በያገባናል ስሜት የሚሳተፉ የተቃዋሚ ድርጅቶች በትብብሩ ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑበት ሁኔታ እንዲመቻች ጥረት ማድረግ
8. በወያኔ እመቃ የተነሳ ባጎራባች ሃገሮችም ሆነ ከዛም በራቁ ስፍራውች መንገላታት ለሚደርስባችው የሃገሪቱ ዜጎች በሙሉ ማናቸውንም አስተዳደራዊ ቁሳዊ እና የሞራል ድጋፍ መስጠት የሚችል ማእከል እንዲመሰረት ወስኗል

ጉባዔው በአንድ ድምጽ
"ሌሎችም ውቅቱ በሚፍጥራችው አስገዳጅ ሁኔታውች ላይ በመመርኮዝ ከቅንጅት አለማቀፍ አመራርም ሆነ የአውሮፓ የድጋፍ ካውንስል የሚቀርቡ የትገል የአፈጻጸም ስልቶችን በሙሉ ቁርጠኝነት ለማስፈጸም፤ ያለንን አቅምና ችሎታ በማስተባበር ገንዘባችንን ጊዚያችንንና ከሁሉም በላይ ለትግሉ ስኬታማነት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሚጠይቀውን ይህይወት መስዋእትነት ያላንዳች ማወላወል ለመክፈል ያለንን ዝግጁነትና ቁርጠኝነት በሙሉ ልብ እናረጋግጣለን" በማለት በተሳካ ሁኔታ ተደምድሟል

ኢትዮጵያውያን ባሉበት ሁሉ ኢትዮጵያ አለች
ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ

ሉቨን መስከረም 17/2006